የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 40
ADDIS ABABA 23 July, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ . ገጽ ፫ሺ፮፻፶፭

CONTENTS

Proclamation No. 534/2007

River Basin Councils and Authorities Proclamation …. Page 3655

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፲፱፻፺፱

## የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ሥርጭቱ በቦታና በወቅት የተዛባ ከመሆኑም በላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ባደገ መጠን የውሃ አጠቃቀም ፍላጎት በመጠንም ሆነ በጥራት እንዲጨምር የማድረግ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ የፖሊሲው ምሰሶ የሆነውን የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር መርህን ተግባራዊ ለማድረግ የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት ማቋቋምን እንደ አንዱና ዋነኛ መሣሪያ አድርጎ የተቀበለው በመሆኑ፣

የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ ውሃ እንደ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ሀብትነቱ ልማቱ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን በተፋሰስ ውስጥ ያሉ አጠቃቀሞች በአጠቃላይ የሚጣጣሙበትን ሥርዓት መዘርጋትን የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ አግባብ ያላቸው አካላት ውሳኔዎቻቸው፣ ዕቅዶቻቸውና ተግባሮቻቸው በውሃው ዑደትና በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ በሚያስከትሏቸው ውጤቶች ላይ የአመለካከት፣ የፍላጎትና የግንዛቤ ልዩነት ቢኖራቸውም ተባብረው እንዲሠሩ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO. 534/2007.

## RIVER BASIN COUNCILS AND AUTHORITIES PROCLAMATION

**WHEREAS,** the distribution of the water resources of Ethiopia is uneven in time and space, and on top of that, the country's economic growth is causing a correlative increase in water uses with quantitative as well as qualitative impacts;

**WHEREAS,** the Ethiopian Water Resources Management Policy, envisages the establishment of river basin councils and authorities as one of the main instruments to implement integrated water resources management which is actually the pillar of the policy;

**WHEREAS**, integrated water resources management requires arrangements for reconciling the different uses of water resources within a river basin to achieve balance and sustainable development of water resources as economic as well as environmental resources;

**WHEREAS**, integrated water resources management process requires that the stakeholders of a river basin shall have to act in a coordinated manner in spite of their differences of approaches, interests and perceptions of the effects of their decisions, plans and activities on the hydrological cycle and on other users;

የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት መቋቋም የተፋሰስ የውሃ ሀብት ዕቅድን መሠረት በማድረግና አግባብነት ባላቸው አካላት ዘንድ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው የጋራ አመራር በማስፈን የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲን በመተግበር ረገድ ብቃት ያለው የተረጋጋ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**ክፍል አንድ**

**ጠ ቅ ላ ላ**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "ተፋሰስ" ማለት ወደ አንድ መልክዓ ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃዎች የሚያካልሉት አካባቢ ሆኖ የሚከተሉትን የኢትዮጵያ ዋና ዋና ተፋሰሶች ከነንዑስ ተፋሰሳቸው ያጠቃልላል፣

ሀ/ የአባይ ተፋሰስ፣

ለ/ የአይሻ ተፋሰስ

ሐ/ የአዋሽ ተፋሰስ

መ/ የባሮ አኮቦ ተፋሰስ

ሠ/ የደናኪል ተፋሰስ

ረ/ የገናሌ ዳዋ ተፋሰስ

ሰ/ የመረብ ተፋሰስ

ሸ/ የኦጋዴን ተፋሰስ

ቀ/ የኦሞ ጊቤ ተፋሰስ

በ/ የተከዜ ተፋሰስ

ተ/ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ፣ እና

ቸ/ የዋቢ ሸበሌ ተፋሰስ።

**WHEREAS**, the establishment of river basin councils and authorities shall have significant contributions in creating efficient and stable mechanisms for the implementation of the Ethiopian Water Resources Management Policy through river basin plans and effective and sustainable joint management by relevant stakeholders of the water resources of the basins;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**PART ONE**

**GENERAL**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "River Basin Councils and Authorities Proclamation No. 534/2007."

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "Basin" means a geographical area, described by the watershed limits of water system including surface and underground water flowing into a common terminus and includes the following main basins and their sub-basins of Ethiopia:

a) the Abbay Basin;

b) the Aisha Basin;

c) the Awash Basin;

d) the Baro-Akobo Basin;

e) the Danakil Basin;

f) the Genale-Dawa Basin;

g) the Mereb Basin;

h) the Ogaden Basin;

i) the Omo-Ghibe Basin;

j) the Tekeze Basin;

k) the Rift Vally Lakes Basin; and

l) the Wabi-Shebelle Basin.

፪/ "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯/፩/ሥር የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፫/ "አግባብ ያለው አካል" ማለት በተፋሰስ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፈልጎም ይሁን ሳይፈልግ የሚሳተፍ ወይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጥቅሙ የሚነካ ማንኛውም ሰው ነው፤

፬/ "የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር" ማለት ውሃ እንደ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሀብትነቱ በተፋሰስ ውስጥ ካሉ የተለያዩ አጠቃቀሞች ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ ሆኖ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው የውሃ ሀብት ልማት እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት ነው፤

፭/ "የውሃ ሀብት" ማለት መጠንና ጥራትን ባካተተ ሁኔታ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ የገፀምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሲሆን የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርንና ረግረጋማ መሬትን ያጠቃልላል፤

፮/ "የውሃ ምደባ" ማለት የተፋሰስን የውሃ ሀብት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ሥርዓትን በመተግበር ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ማከፋፈል ነው፤

፯/ "የውሃ ግልጋሎት" ማለት በውሃ ሀብቱ ወይም ውሃው ሊሰጠው በሚችለው ግልጋሎት ወይም በውሃው የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም የውሃ አጠቃ ቀም ሲሆን ውሃውን መውሰድን፣ የውሃውን ተፈጥሮአዊ መሄጃ ማሻሻልንና የታከመ ቆሻ ሻን ለመድፋት፣ ለመዝናኛ፣ ለዓሣ እርባታ፣ ለውሃ ላይ ትራንስፖርትና ለሌሎች አገልግ ሎቶች ማዋልን ያጠቃልላል፤

፰/ "የተፋሰስ ዕቅድ" ማለት በውሃ ሀብት አጠ ቃቀም ፍትሐዊነትንና ቀጣይነትን በማረ ጋገጥ ዓላማ ላይ የተመሠረተና የረዥም ጊዜ ራዕይ ያለው ስትራቴጂክ የተፋሰስ የውሃ ሀብት ዕቅድ ነው፤

፱/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የውሃ ሀብት ሚኒስ ቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

2/ "Regional State" means any regional state specified under Article 47 (1) of the Constitution and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

3/ "Stakeholder" means any person who is deliberately or unintentionally involved in, or directly or indirectly affected by, water resources management in a basin;

4/ "Integrated Water Resources Management" means an arrangement for balanced and sustainable development of water, as an economic, social and environmental resource, reconciling, fully, its various uses within a river basin;

5/ "Water Resources" means the availability, both in quantity and quality of surface and ground water in a river basin including aquatic ecosystems and wetlands;

6/ "Water Allocation" means a system of sharing the water available in a basin among various users according to water use permit;

7/ "Water Use" means any utilization of water likely to have an impact either on the water resources and its availability to other uses or on the aquatic ecosystems, and includes abstraction of water, modification of the natural water course, use of water to discharge pollutants and use of water for recreational, fisheries, navigation and other activities;

8/ "River Basin Plan' means strategic water resources planning with long-term vision in the aim of guarantying equity and sustainability in water resource uses;

9/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of water Resources, respectively;

11/ "Person" means any natural or juridical person.

## ክፍል ሁለት

## ስለተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት

### ፫. መቋቋም

፩/ የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጡ ደንቦች ይቋቋማሉ።

፪/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተፋሰሶች በአንድ ከፍተኛ የተፋሰስ ምክር ቤትና ባለሥልጣን ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

### ፬. ዓላማ

የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አጠቃላይ ዓላማ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ፍትሐዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ ለሕዝብ የሶሺዮ ኢኮኖሚ ብልጽግና በሚያመጣና የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር ቀጣይነትን ባረጋገጠ ሁኔታ የሥልጣን ክልላቸው በሆነው ተፋሰስ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማበረታታትና መቆጣጠር ይሆናል።

### ፭. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት አባላት

፩/ የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ይመደባሉ።

፪/ የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ተጠሪነት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

### ፮. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት

የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ በተፋሰሱ ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት መካከል በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር አተገባበር ረገድ ከፍተኛ ቅንጅታዊ አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫና በዕቅድ ችግሮች ላይ አመራር ይሰጣል፤

፪ የተፋሰሱን ዕቅድ ዝግጅት ይመራል፣ ለመንግሥት አቅርቦ ያስጸድቃል፤

## PART TWO

## RIVER BASIN HIGH COUNCILS AND AUTHORITIES

### 3. Establishment

1/ River Basins High Councils and Authorities shall be established by Regulations to be issued by the Council of Ministers.

2/ When it is deemed necessary, two or more river basins may be under the jurisdiction of a single Basin High Council and Authority.

### 4. Objectives

The overall objectives of river basin High Councils and Authorities shall be to promote and monitor the integrated water resources management process in the river basins falling under their jurisdictions with a view to using of the basins' water resources for the socio-economic welfare of the people in an equitable and participatory manner, and without compromising the sustainability of the aquatic ecosystems.

### 5. Members of Basin High Councils

1/ A Basin High Council members shall be designated by the Government.

2/ The accountability of a Basin High Council Shall be determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers.

### 6. Powers and Duties of Basin High Council

A Basin High Council shall have the powers and duties to:

1/ provide policy guidance and planning oversight to ensure high level of coordination among stakeholders for the implementation of integrated water resources management in the basin;

2/ direct the preparation of the river basin plan and submit same for approval by the Government;

፫/ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ተጠቃሚ ዎች ሊከፍሉት የሚገባውን የክፍያ መጠን በተመለከተ ለመንግሥት ሃሣብ ያቀርባል፤

፬/ በተፋሰሱ ውስጥ ከፍተኛ የውሃ ነክ ሥራ ዎች ግንባታንና የቅደም ተከተሉን አግባ ብነት በመመርመር ይወስናል፤

፭/ በተፋሰሱ የውሃ እጥረት በሌለበትና ባለበት እንዲሁም በድርቅ ወይም በጎርፍ ጊዜ ሊኖር የሚገባውን የውሃ ምደባ ሥርዓትና መርህ ተገቢነት በመመርመር ይወስናል፤

፮/ ተፋሰሱን በሚጋሩ ክልሎች መካከል የውሃ ሀብት አጠቃቀምን በሚመለከት ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይሰጣል፤

፯/ ተፋሰሱ የወሰን ተሻጋሪ ተፋሰስ አካል ከሆነ ከጎረቤት አገሮች ጋር ይህን በሚመለከት የመወያየት ኃላፊነት ላለበት አግባብ ያለው አካል የመረጃና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

፰/ የተወሰነ ዓላማን ለማስፈፀም የሚረዱ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

## ፯. <u>የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ስብሰባዎች</u>

፩/ የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት በዓመት ቢያ ንስ ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳ ቢው በራሱ አነሳሽነት ወይም በ፩/፫ኛ የምክር ቤቱ አባላት በጋራ ጥያቄ ሲቀርብ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፫/ ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሣብ የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።

፬/ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

3/ propose to the Government the rate of the water charges to be paid by water users in the basin;

4/ examine and decide on the appropriateness and prioritization of constructing major water works in the basin;

5/ examine and decide on water allocation rules and principles in normal times and in times of water shortage as well as in times of drought or flooding;

6/ manage water use disputes between Regional States in the basin;

7/ provide information and advisory support to the body in charge of negotiating with neighboring countries with respect to the basin where the basin is part of a trans boundary basin;

8/ establish standing or ad-hoc committees necessary for discharging specific activities.

## 7. Meetings of Basin High Councils

1/ A Basin High Council shall hold regular meetings at least twice in a year; provided, however, that the Chairperson may, on his own initiative or upon the joint request of three members, call extraordinary meeting to be held at any time.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Council are present at a meeting.

3/ The Council shall pass decisions by majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ In the absence of the Chairperson, the Vice-Chairperson shall preside over the meetings of the Council.

5/ The Council may, without prejudice to the provisions of this Article, adopt its own rules of procedure.

## ፰. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ሴክሬታሪያት

የተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል።

## ፱. የተፋሰስ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር

የተፋሰስ ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፪/ በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፫/ በተፋሰሱ ውስጥ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶች፣ ተግባሮችና መስተጋብሮች በይዘታቸው፣ በጊዜ ሠሌዳቸው፣ በውጤታቸውና በአመራራቸው ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፬/ የተፋሰስ ዕቅድ በማዘጋጀት ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፭/ ለክልሎች በሕግ የተሰጠ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሱ ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ይሰጣል፣ በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

፮/ በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሠራጫል፣

፯/ የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፣

፰/ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን ስለሚመለከቱ አለመግባባቶች አፈታት ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና ለሚኒስቴሩ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

## 8. Secretariats of Basin High Councils

A Basin Authority shall serve as the secretariat of the respective Basin High Council

## 9. Powers and Duties of Basin Authorities

A Basin Authority shall have the powers and duties to.

1/ initiate and submit to the Basin High Council policy measures needed to create a conducive environment for the implementation of an integrated water resource management process within the basin; and follow up the implementation of same upon approval;

2/ undertake activities necessary for, and facilitate, the implementation of integrated water resources management in the basin;

3/ ensure that projects, activities and interventions related to water in the basin are, in their content, schedule, impacts and management are in line with the integrated water resources management process;

4/ prepare, and submit to the Basin High Council, the basin's plan and monitor its implementation upon approval;

5/ without prejudice to the power given to Regional State by law, issue permits applicable to the basin's water use and water works in accordance with Article 15 of this Proclamation, and ensure that the terms of the permits are complied with;

6/ collect, compile, analyze and disseminate information for proper planning, administration and steering of water resources in the basin;

7/ develop and use a river basin model in order to guide and support its basin water resources strategic planning and water administration functions;

8/ give advice and technical support to the Basin High Council and the Ministry on dispute resolution in relation to the allocation and use of water resources of the basin;

፱/ አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ውጤታማ የግ ንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

፲/ ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ ይሰበስባል፤

፲፩/ ከሌሎች አገሮች ጋር ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ለመወያየት አግባብ ላለው አካል በተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት መመሪያ መሠረት አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤

፲፪/ ተግባሮቹን ለማከናወን የሚረዱ ጥናቶ ችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያካሂዳል፤

፲፫/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋ ላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፬/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ፲. የተፋሰስ ባለሥልጣን ተጠሪነት

የተፋሰስ ባለሥልጣን ተጠሪነት፣

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት፣ እና

፪/ በሥልጣንና ተግባሩ ሥር የሚወድቁ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ለሚኒስቴሩ፣

ይሆናል።

## ፲፩. የተፋሰስ ባለሥልጣን አቋም

የተፋሰስ ባለሥልጣን፣

፩/ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፪/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

## ፲፪. የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

፩/ የተፋሰስ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር የባለ ሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የባለ ሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳ ድራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለ ከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣

9/ set up a forum for effective networking among stakeholders;

10/ collect water charges from users;

11/ on the basis of instructions of the Basin High Council, prepare and provide necessary information for the concerned body in charge of negotiations with other countries concerning trans-boundary river basins;

12/ undertake studies, surveys and researches that are deemed necessary to carry out its functions;

13/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

14/ carry out other functions necessary for the implementation of its objectives.

## 10. Accountability of Basin Authorities

A Basin Authority shall be accountable:

1/ to the respective Basin High Council with respect to issues falling under the provisions of Article 6 of this Proclamation; and

2/ to the Ministry with respect to other issues falling under its jurisdiction.

## 11. Organization of Basin Authorities

A Basin Authority shall have:

1/ a Director General to be appointed by the Government upon the recommendation of the Minister; and

2/ the necessary staff.

## 12. Powers and Duties of Director Generals

1/ The Director General of a River Basin Authority shall, as the chief executive of the Authority, direct and administer the activities of the Authority.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ላይ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ መንግሥት በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

መ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ሠ/ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ረ/ በተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና በሚኒስቴሩ በየጊዜው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ይፈጽማል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ፲፫. በጀት

የተፋሰስ ባለሥልጣን በጀት በፌደራል መንግሥት ከሚመደብ ገንዘብና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱/፲/ መሠረት ከሚሰበሰብ የውሃ ክፍያ የተውጣጣ ይሆናል።

## ፲፬. የሂሣብ መዛግብት

፩/ የተፋሰስ ባለሥልጣን የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የተፋሰስ ባለሥልጣን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

a) exercise the powers and duties of the Basin Authority specified in Article 9 of this Proclamation;

b) employ and administer the employees of the Basin Authority in accordance with directives to be issued by the Government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Basin Authority;

d) represent the Basin Authority in all its dealings with third parties;

e) prepare and submit to the Basin High Council and to the Ministry the annual operational and financial reports of the Basin Authority;

f) carry out any other duties required by the Basin High Council and the Ministry.

3/ The Director General may, to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Basin Authority, delegate part of his powers and duties to employees of the Authority.

## 13. Budget

The budget of a River Basin Authority shall be drawn from funds allocated by the Federal Government and water charges to be collected pursuant to Article 9(10) of this proclamation.

## 14 Books of Accounts

1/ A Basin Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of a Basin Authority shall be audited annually by the Auditor General or by an Auditor designated by him.

## ክፍል ሦስት
## የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ፣ የመረጃ ሥርዓትና የተፋሰስ ዕቅድ

### ፲፭. የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ

፩/ የተፋሰስ ባለሥልጣን በውሃ የመጠቀምና የውሃ ነክ ሥራዎችን በሚመለከት ፈቃድ የሚሰጠው የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተ ዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፯/፲፱፻፺፪ እና የደንብ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺፯ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፪/ የተፋሰስ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሰጣቸውን ፈቃዶች በሚመለከት የተጠናቀረ መረጃ ለሚኒስቴሩ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

፫/ በውሃ ለመጠቀም ወይም ውሃ ነክ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ አሠጣጥ ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት አንፃር የተፋሰሱን የወደፊት ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

### ፲፮. የተፋሰስ የመረጃ ሥርዓት

፩/ ማንኛውም የተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድንና የውሃ ሀብት አስተዳደር ተግባራትን ሊመራና ሊደግፍ የሚችል አስተዳደር ተኮር የተፋሰስ መረጃ ሥርዓት ማደራጀትና መጠቀም አለበት።

፪/ የተፋሰስ የመረጃ ሥርዓት ቢያንስ የሚከ ተሉትን ቁልፍ አመልካቾች ማካተት ይኖርበታል፤

ሀ/ የተፋሰሱን የውሃ ሀብት መጠንና ጥራት፤

ለ/ የተፋሰሱን የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር፤

ሐ/ በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ ፍላጎት መጠን፤

መ/ ነባርና ለወደፊቱ የታቀዱ ዋና ዋና መሠረተ ልማቶችን፤

ሠ/ በውሃ ሀብቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዋና ዋና ጣልቃ ገብ ሥራዎ ችን ወይም ፕሮጀክቶችን፣

ረ/ በሥራ ላይ ያለውን የውሃ አጠቃ ቀም፣ እና

## PART THREE
## WATER USE PERMITS, INFORMATION SYSTEM AND RIVER BASIN PLANS

### 15. Water Use Permits

1/ A River Basin Authority shall give permits relating to water use and water works in compliance with the provisions of the Ethiopian Water Resources Management Proclamation No. 197/2000 and Regulations No. 115/2005.

2/ A River Basin Authority shall have the duty to transmit to the Ministry information compiled with respect to the issuance of permits pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

3/ The issuance of permits relating to water use or water works shall take into consideration the basin's future perspective in line with integrated water resources management process.

### 16. Basin Information System

1/ Every River Basin Authority shall develop and use management oriented basin information system, in order to guide and support the basin water resources strategic planning and water management functions.

2/ A basin information system shall encompass at least the following key indicators:

a) the quantity and quality of water resources of the basin;

b) the aquatic ecosystem of the basin;

c) the level of the water demand within the basin;

d) the existing and planned major water infrastructures;

e) the main interventions or projects that may have impact on the water resources;

f) the existing water uses; and

ሰ/ የተፋሰሱን አግባብ ያላቸው አካላት።

፫/ የተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰስ የመረጃ ሥር ዓት ሲያደራጅም ሆነ ሲጠቀም በፌደራል ደረጃ ሊኖር ስለሚገባው የመረጃ መጣጣም ጉዳይ ተገቢ ትኩረት መስጠት አለበት።

## ፲፯. የመረጃ ልውውጥ

፩/ የተፋሰስ ባለሥለጣን በተፋሰስ የመረጃ ሥር ዓት ውስጥ የሚገኝ መረጃን አግባብ ላላቸው ሁሉ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መስጠት አለበት።

፪/ ማንኛውም ሰው ለተፋሰስ ባለሥልጣን የመረጃ ሥርዓት የሚጠቅሙ ከውሃ ጋር ተያ ያዥነት ያላቸው መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ የመስጠት ግዴታ አለበት።

፫/ የተፋሰስ ባለሥልጣን በተፋሰሱ ውስጥ ብቃት ያለው የመረጃ ቁጥጥር መረብ ለመዘርጋትና ለማሻሻል አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር ተባብሮ መሥራት አለበት።

፬/ የተፋሰስ ባለሥልጣን የራሱን የመረጃ ቁጥጥር መረብ ለማቋቋምና ለማካሄድ ይችላል።

## ፲፰ የተፋሰስ ዕቅድ

፩/ የተፋሰስ ባለሥልጣን በተፋሰሱ ውስጥ ፍትሐዊ የውሃ ክፍፍልን፣ ቀጣይነት ያለው ልማትንና የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርን የማያዛባ የውሃ ሀብት አጠቃቀምን የሚያረጋግጥ ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል የውሃ ሀብት አስተዳደር ማዕቀፍ እንዲኖር የሚያስችል የተፋሰስ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል።

፪/ የተፋሰስ ዕቅድ፣

ሀ/ የተፋሰሱን የውሃ ሀብት፣

ለ/ የተፋሰሱን እንክብካቤ፣

ሐ/ በውሃ ሀብቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን፣

መ/ በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ አጠቃቀም ደረጃ የሚያሳይ አኃዛዊ መግለጫ፣

ሠ/ የተፋሰሱን የወደፊት ሁኔታ አቅጣጫ ሊያሳይ የሚችል ትንታኔ፣

g) stakeholders of the basin.

3/ A River Basin Authority shall have to address adequately the issue of data harmonization at federal level, while developing and using the basin information system.

## 17. Information Exchange

1/ A river Basin Authority shall, in accordance with directives to be issued by the Ministry, provide stakeholders with information contained in the basin information system.

2/ Any person shall have the duty to provide a river Basin Authority with information that is found useful for the basin information system.

3/ A river Basin Authority shall cooperate with the relevant federal and regional bodies for the installation and improvement of effective data monitoring networks in the basin.

4/ A River Basin Authority my develop and run its own data-monitoring network.

## 18. River Basin Plans

1/ A River Basin Authority shall have a river basin plan, in order to provide a long-term framework for proper water resources management in the basin that will ensure equitable sharing, sustainable development and use of water resources while maintaining the quality of aquatic ecosystems.

2/ A river basin plan shall contain:

a) analysis of available water resources in the basin;

b) watershed management;

c) identification of significant pressures on water resources;

d) quantification of the current and future level of water use in the basin;

e) trend analysis depicting possible futures for the basin;

ረ/ በሁኔታዎች ግምገማ ላይ የተመሠረተና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት አተገባበርን ዕውን ለማድረግ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን፣ እና

ሰ/ ዕቅዱን የሚተገብሩ አካላትን፣ የድርጊት መርሐ ግብርንና የሚያስፈልገውን በጀትን ጨምሮ ዕቅዱን ተግባራዊ የማድረጊያ ዘዴዎችን፣

ማካተት ይኖርበታል።

፫/ በተፋሰሱ ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት የሚከናወኑ ከውሃ ጋር ተያያ ነት ያላቸው ተግባራት ከተፋሰስ ዕቅዱ ጋር እንዲጣጣሙ መደረግ አለባቸው።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፱. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በተመለከተ ከተፋሰስ ባለስልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

### ፳. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

### ፳፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስ ፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል።

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

### ፳፪. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

f) based on the situation analysis, strategic orientations for actual implementation of integrated water resources management process;

g) means of implementing the plan, including implementing actors, action plans and budget requirement;

3/ Water related activities of stakeholders in the basin shall be made compatible with the basin plan.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 19. Duty to Cooperate

Any person shall have the duty to cooperate with a River Basin Authority in the implementation of this Proclamation.

### 20. Inapplicable Laws

No law shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

### 21. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the execution of this Proclamation.

2/ The Ministry shall issue directives necessary for the execution of this Proclamation.

### 22. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 23 day of July, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**